# የሽግግር መንግስት ማቋቋም ሂደት፣

በኢትዮጵያ ሊከሰቱ የሚችሉትን ቢሆኖች ካየን በኋላ አካታችና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ስርዓት ለመፍጠር ምን ይደረግ በሚለው ላይ የሁሉም ትኩረትና አስተዋጽኦ ይጠይቃል። ኢትዮጵያን የማዳን መድረክ ለዚሁ መነሻ ሊሆን ይችላል ያለውን ፍኖተካርታ እንደሚከተለው ያቀርባል።

**የሽግግር መንግስት የሚመሰረተው የለውጥ ሃይሉ አሸናፊ ሆኖ ሲወጣ ወይም መንግስትን በማስገደድ ወደ ድርድር ሲመጣ ነው።** የለውጥ ሃይሉ አካታችና አሳታፊ መሆን እንዳለበት ቀደም ሲል ተገልጿል። የለውጥ ሃይሉ ስንል ኢትዮጵያዊነትንና አንድነትን የተቀበሉ፣ ለፍትህና ለሰላም እንዲሁም ለዲሞክራሲ የሚታገሉትን የተለያዩ የታጠቁ ሃይሎችን፣ ክልሎችን እና የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተ ግንባር ማለት ነው። **ይህ ግንባር በውስጡ ወይም በጋራ ከመንግስት ጋር በሚያደርገው የስልጣን ክፍፍል በሽግግር ጊዜ የህግ አስፈጻሚነትን (executive)ተግባር ይፈጽማል።** የፍትህ አካሉ(judiciary) በነጻነት እንዲሰራ ይደረጋል። ፓርላማው ፈርሶ በሽግግር ወቅት የሚቋቋም ጊዚያዊ ህዝባዊ ሸንጎ ይኖራል። ህዝባዊ ሸንጎ በሽግግር ወቅት የሚያስፈልጉትን ህጎች ያጸድቃል። በህገመንግስቱ ለሽግግሩ እንቅፋት የሚሆኑትን አንቀጾች ያስተካክላል ወይም ያነሳል። ለመደበኛ ፓርላማ ምርጫን አስመልክቶ የሚያስፈልጉ ህጎችና አሰራሮችን ያወጣል። መደብኛ ፓርላማ ሲመረጥ ጊዚያዊ ህዝባዊ ሸንጎ ስራውን ያቆማል። የለውጥ ግንባሩም በፓርላማ ለሚመረጠው መንግስት ስራውን ይለቃል።

የለውጥ ግንባሩ የሽግግር ሸንጎ እስኪመሰረት ድረስ የመንግስት ስልጣኑን ይዞ እንደ ሞግዚት መንግስት ይሰራል። የሞግዝት መንግስት ስራና ሃልፊነት በዚሁ ሰነድ መጨርሻ ላይ ተገልጿል።

ግዚያዊ ህዝባዊ ሸንጎ ለማቋቋም **አገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ሃይል** ይቋቋማል። ይህ አካል የለውጥ ግንባሩ በሰየመው ኮሚቴ /**አሰባሳቢ ኮሚቴ**/ ይቋቋማል። የሚከተለውን ቅደም ተከተል ይዞ ይሂዳል፣

## 1. አሰባሳቢ ኮሚቴ

- በለውጡ ግንባር (በሞግዚት መንግስቱ) ይሰየማል
- የስራ መመሪያውን ያዘጋጃል፣
- ለስራ ማስኬጃ የሚሆን በጀት ከሞግዚት መንግስቱ ይጠይቃል፣
- በአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉ አካላት/አባላት የምርጫ መስፈርት ያዘጋጃል፣ ለአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል የሚመጥንና የሚሆን መታዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣ ጊዜው ሲደርስም፣ በግብረ ኃይሉ እንዲጸድቅ ያስደርጋል፣
- የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉ ዓላማና ግብ ምን እንደሆነ የሚዘረዝር ሰነድ ያዘጋጃል፣
- በመስፈርቱ መሰረት የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ተወካዮች ተመርጠው ቃለ መሃላ ይፈጽማሉ፣ኃላፊነት ተከፋፍለው ስራ ይጀምራሉ።
- የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል ስለመቋቋሙና ስለሚያከናውናቸው ተግባሮች ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ያሳውቃል። ተቋሙን እንዲተባበሩት ያሳስባል። ከዚያም ይህ አካል ራሱን ያከስማል።
- ግብረ ኃይሉ ከፈለገው ይህ አካል በአማካሪነት ሊቆይ ይችላል።

## 2. አገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ሃይል

የአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይል፣ ከመንግስት፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከታጠቁ ኃይሎች፣ ከሲቪል ማህበራት፣ ከብዙሃን ድርጅቶች፣ ከእምነት ተከታዮች፣ በውጭ ሀገራት ከሚገኙ የኢትዮጵያውያን ድርጅቶችና ከሌሎች በፈቃደኛነት ከተሰባሰቡ ሀገር ወዳድ ዜጎች፣ ምሁራንና ከሌሎች ይመሰረታል።

የግብረ ኃይሉ የስራ ዘመን ከ6 ወራት የማይበልጥ ይሆንና፤ ሦስት ወቅቶች ይኖሩታል፣

ወቅት 1 - የቅድሚያ ወቅት (የሚወስደው ጊዜ ይወሰናል)
ወቅት 2 - የመካከለኛ ጊዜ ወቅት (የሚወስደው ጊዜ ይወሰናል) |
ወቅት 3 - የረዥም ጊዜ ወቅት (የሚወስደው ጊዜ ይወሰናል)

- **ወቅት 1- የቅድሚያ ወቅት ተግባሮች፣**
  - **አገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉ፣ በህዝብ የተወከለ አገራዊ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል፣ በዚያውም አገራዊ ሸንጎ ያቋቁማል።**
  - ለጉባኤው የውይይት አጀንዳ ያዘጋጃል፣
  - ጊዜያዊ የመተዳደሪያ ደንቡ በጉባኤው እንዲጸድቅ ያደርጋል፣
  - ለሽግግር ወቅት የሚያስፈልጉ ህጎችና መመሪያዎች በአገራዊ ሸንጎ እንዲጸድቁ ያደርጋል።
  - ግብረ ኃይሉ ሊያከናውናቸው የሚገባቸውን ዝርዝር የስራ መመሪያዎች በጉባኤው ያስጸድቃል፣
  - ግብረ ኃይሉን ሊረዱ የሚችሉ ባለሙያዎች ይመለምላል/ይመርጣል፣
  - አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ውሳኔዎችንም ያደርጋል።
  - ውይይቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድና እንዲገባደድ፣ ለአገራዊ መፍትሔ አፈላላጊ ግብረ ኃይሉ ልዩ ጥበቃ የሚያደርግ ተቋም ይመሰረታል፣
  - የሽግግር ጊዜ ህጎቹና ደንቦቹ በአገራዊ ሸንጎ የሚጸድቁ ሲሆኑ፣ የሚከተሉት ኃላፊነቶችንና ሌሎችን የሚዳስሱ ይሆናሉ፣
    - የስራ አስፈጻሚውን ስልጣን፣
    - የሽግግር መንግስት ምስረታ አስፈላጊነትና ምክንያቱ ላይ ተወያይቶ በተደነገገው መተዳደሪያ መሰረት ውሳኔ ላይ መድረስ፣
    - የሽግግር መንግስቱን ስለሚመሰርቱት አባላት መስፈርት ማዘጋጀት፣ ከዚያም፣

      1. የሽግግር መንግስት ምስረታንና የሚቆይበትን ጊዜ መተለም፣
      2. የሀገራዊ ምርጫ ጊዜውን በተመለከተ መመሪያ ማዘጋጀት፣
      3. የምርጫ ቦርድ ኃላፊነትን በተመለከተ መመሪያ ማዘጋጀት፣
      4. የፍትህ ሥርዓቱን ስለማሻሻል፣
         - በህገ መንግስቱ ከተደነገገው ውጭ የታሰሩ ሰዎችን በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይደረጋል፣ ያ ሳይሆን ከቀረ የሚመለከተው አካል ተጠያቂ ይሆናል፣
         - የመከላከያና ሌሎች የወታደራዊ ኃላፊዎች ኃላፊነትንና ተግባርን በተመለከተ መመሪያ ያዘጋጃል፣
         - ህገ መንግስቱን ስለማሻሻል መመሪያ ያወጣል፣
         - ኢመደበኛ ወታደራዊ አካላትን በተመለከተና በሌሎች ጉዳዮች ላይ መመሪያዎች ዘጋጃሉ።

- **ወቅት 2 - የመካከለኛ ጊዜ ተግባሮች**
  - ይህ ወቅት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ይወሰናል፣
  - በዚህ ዘመን ሕገ መንግሥት ይቀረጻል፣ የመንግሥት ተቋማት ሥራቸውን በግልጽነትና በታማኝነት (በፖለቲካ አባላት ሳይሆን) በቴክኖክራቶች መሪነት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፣
  - ሀገራዊ ምርጫ ለማካሄድ፣
  - የምርጫ ቦርድን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣
  - ምርጫን በተመለከተ ተዛማጅ መመሪያዎች ያሰናዳል፣
  - የምርጫ ጊዜውን ይወስናል፣
  - ስለምርጫው ሂደት መመሪያ ያዘጋጃል፣
  - ስለ መራጮች ምዝገባ የጊዜ ገደብ ይወሰንና ይፋ ይደረጋል፣
  - ስለፓርቲ አደረጃጀት፣ በተለይም በማንነትና በሃይማኖት ስለመደራጀት መመሪያ ያዘጋጃል፣
  - የምርጫ ቦርድ ደንብ መሥፈርት የሚያሟሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝብ ምርጫ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፣
  - የሕዝብ ተወካዮች ለአገራዊና ለሕዘባዊ ውክልና በግልፅነትና በምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት ይወዳደራሉ፣
  - የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራዊ ምርጫው በነፃ ስለሚወዳደሩበት ብልሃት፣ አገራዊ ራዕያቸውን ስለማስረዳት፣ የሕዝባዊ መገናኛዎችን ፍትሃዊና በእኩልነት ስለመጠቀም፣ ወዘተ መመሪያ ይዘጋጃል፣
  - ስለ መንግስት ሠራተኞች ቅጥር፣
  - የመንግሥት ሠራተኞች የሚቀጠሩት በትምህርት፣ በተመክሮ፣ በፈተናና በሥራ ብቃታቸው ብቻ ይሆናል፣
  - ለሥራ የሚቀጠሩትም በሥራ ቦታ ክፍትነት ላይ የተመረኮዘ ብቻ ይሆናል። የሥራ መደራረብ (duplication) እንዳይኖርና ገንዘብና የሰው ኃይል እንዳይባክን ጥንቃቄ ይደረጋል፣

- ባለፉት አምስት ዓመታትና ከዚያም በፊት የተቀጠሩት በሥራ ብቃታቸው ሳይሆን በማንነታቸው ብቻ ከሆነ ድጎማ እየተሰጣቸው ከሥራቸው ይሰናበታሉ። ክፍት የሥራ ቦታ ካለ እንደማንኛውም አመልክተው ካለፉ የመቀጠር ዕድል ይሰጣቸዋል፣
- በዚህ መሰረት እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት እራሱን እንዲገመግም፣ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠበቃል፣· በህዝብ መካከል የሚደረገው ውይይትና ትምህርት ይቀጥላል፣ ለዚህም መንግሥትና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶች፣ ተቋማትና በተለይም የኢትዮጵያውያን ሁሉ ትብብርና ርብርቦሽ አስፈላጊነት ወሳኝ ነው።
- ምሁራን፣ ተመክሮ ያላቸው ግለሰቦች፣ አዛውንቶችና ሌሎችም (ህዝባዊ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ህዝባዊ መገናኛዎች፣ ወዘተ) ህዝቡን በማስተማር፣ በማንቃትና አቅጣጫ በመስጠት እዲሳተፉ ይጋበዛሉ።
- በአንገብጋቢ አገራዊ ጥያቄዎች ዙሪያ (የሀገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ስለክልል/ክፍለሀገሮች አደረጃጀት፣ ስለአገራዊ ቋንቋ፣ ኢትዮጵያን ስለማዳን፣ ወዘተ) ውይይት ያካሄዳል።
- በዚህ መሠረት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የህዝቡን ሐሳብ፣ ፍላጎትና ራዕይ አጥንተው (opinion survey) ውጤቶቻቸውን ለአገራዊ ጉባኤው እንዲያቀርቡና እንዲተነትኑ ይጠየቃሉ፣ መፍትሔም ይጠቁማሉ፣

- ***ወቅት 3 - የሩቅ ጊዜ ተግባሮች***

***የሀገራዊ ሸንጎ ምስረታና ተግባር***

ብዙውን ጊዜ ይህ አካል የሚፈጠረው አሮጌ ስርዓት በአዲስ በሚታከበት ወቅት ሲሆን፣ አዲስ የሚወለደው አስተዳደር የሚተዳደርበትንና የሚገዛበትን ህጎች ይነድፋል፣ ሥርዓትም ይዘረጋል፡፡ ይህ ሸንጎ አካታች ከመሆኑ ባለፈ፣ መላ ሕብረተሰብ በመረጠው ወኪል አማካኝነት በአንድ አዳራሽ ተሰብስቦ የወደፊት ዕጣ ፈንታውን የሚወስንበት አጋጣሚ ነው፡፡ ይህ አካል፣

- ሁሉም የሕብረተሰብ አካላት በምርጫ፣ በመረጣቸው ወይም በሌላ ዘዴ ድምፃቸውን ሊያሰሙላቸው የሚችሉ አባላትን መርጠው ለአባልነት ይልካሉ፣
- ሀገራዊ ሸንጎው፣ አሳታፊ የሆነ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣ ለምሳሌ፣
- የሚነሱ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች በቀላል የድምጽ አሰጣጥ ይወሰናሉ፣
- ከበድ ያሉና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች ተለይተው ከወጡ በኋላ በከፍተኛ የድምጽ ቁጥር እንዲወሰኑ ይደረጋል፣
- ግልጽነትና መተማመን እንዲኖር የሚረዱና ሌሎች ህጎች በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ይካተታሉ፣
- የሀገራዊ ሸንጎው ዋነኛ ኃላፊነት ሀገሪቱ የምትተዳደርበትን ህገ መንግስት ነድፎ ስራ ላይ ማዋል ይሆናል፣
- ሕብረተሰቡ ሰፊ ግንዛቤና ትምህርት እንዲያገኝ፣ ሀገራዊ ሸንጎው ጠቃሚና አስፈላጊ ባላቸው ሀገራዊ ጥያቄዎች ላይ ውይይቶች፣ ትምህርቶች፣ ክርክሮች፣ ወዘተ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ · የህገ መንግስቱ ረቂቅ በሁለት መንገድ ሊዘጋጅ ይችላል፣
- አስቀድሞ ህብረተሰቡን በማሳተፍ በህገ መንግስቱ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ሃሳቦችን በመሰብሰብ፣ ወይም፣
- ባለሙያዎች አሰማርቶ ረቂቅ ህጉን ማሰናዳት፣
    - ረቂቁ ለሀገራዊ ሸንጎ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ህገ መንግስቱ ይጸድቃል፣.
    - ሀገራዊ ሸንጎው፣ በስራው ሊረዱት የሚችሉ የተለያየ ሙያና ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎች ይኖሩታል፣
    - በመጨረሻም፣ ሀገራዊ ሸንጎው የወሰነባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ለህዝበ-ውሳኔ ቀርበው ህዝብ ይወስንባቸዋል፡፡
    - ሀገራዊ ሸንጎው ስለ አገር አንድነትና ስለአንዳንድ ጉዳዮች ወሳኝ መመሪያ ያወጣል፣
    - የውጪ ግንኙነትን በተመለከተ በሽግግሩ ዘመን በውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በኩል ቋሚ በሆኑ ዲፕሎማቶች (career diplomats) መሪነት ለጎረቤት አገሮች፣ ለአፍሪካ አንድነትና ሚመለከታቸው ሁሉ በየጊዜው ገለጻ ይደረግላቸዋል፣
    - አገራዊ ጉባኤ አዘጋጆችና ጊዜያዊ የተቋማት አስተዳዳሪዎች (technocrats) የሽግግሩ መንግሥት ሲያበቃና ቋሚ መንግሥት ሲመሰረት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያከትማል።
    - የፖሊስና የፀጥታ ኃይሎች ከህዝብ ጋር በመተባበር እንዲሰሩ ይደረጋል፣

- ከላይ የተጠቀሱት አንዳንዶቹ ተግባራት፣ በጥቂት ወራት ውስጥ ስለማይፈጸሙ በቀጣይነት እንዲሰራባቸው ይደረጋል።

<u>የሞግዚት መንግስት በሚመለከት፤</u>

አሁን በሚታየው ሂደት የስርዓት/የመንግስት ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች መንግስትን አስገድደው ለድርድር እንዲቀርብ ካልሆነም በኃይል ሊያስወግዱት እንደሚችሉ ነው። እነዚህ ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች በጋራ የተቀናጀ ፕሮግራም ባይኖራቸውም መንግስት ላይ በሚያደርሱት ጥቃት ሊወድቅ እንደሚችል ይታያል። መንግስት አልባ የምትሆነው

ኢትዮጵያ ለከፋ አደጋ ልትጋለጥ ትችላለች። በውጭ ጠላቶችም የመደፈር ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በየክልሉ በሚገኙ ወታደራዊ ኃይሎች መካከል ግጭት ተፈጥሮ መረጋጋት ደብዛው ሊጠፋ ይችላል፣ ግድያ፣ የግጭቶች መበራከትና የተዛማጅ ችግሮች መስፋፋት ዜጎችን ክፉኛ ለማወክ ይችላል። የተዳከመው ኤኮኖሚ የበለጠ ይዳሽቃል፤
የአገሪቱ ሁኔታም የባሰውን ምስቅልቅሉ ይወጣል። ሰላም ጨርሶ ይጠፋል። እነዚህና ሌሎች መሰል ሁኔታዎች ሁሉ ተደማምረው የኢትዮጵያን ችግር ክፉኛ ያባብሳሉ። መዘዙ ስር ሰዶ ሀገሪቱን ለከፋ አለመረጋጋትና ለበለጠ መከፋፈል ይዳርጓታል።

ይህን መንግስት የሚተካ አካል አስቀድሞ ባልተዘጋጀበት ሁኔታ የሀገሪቱ ቀውስ መፍቻ ወደሌለው ሥርዓተ አልበኝነትና ሁሉም በሁሉም ላይ ወደሚነሳበት አገር አፍራሽ ሂደት ውስጥ ልትገባ ትችላለች። ሂደቱ መቼ እንደሚጀመር መተንበይ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ማስቆሙ ግን እጅግ ከባድ እንደሚሆን መገንዘብ ከባድ አይደለም።

ኢትዮጵያ ለአንድም ቀን እንኳን ቢሆን መንግስት አልባ ሆና መዋልና ማደር አይኖርባትም። መጪው ሁኔታ አደገኛና አሳሳቢ በመሆኑ፣ ጊዜ ሳይባክን ኢትዮጵያን የማዳን አስፈላጊ ዝግጅቶች ማካሄድ የዜጎች ዋነኛ አጀንዳ ሊሆን ይገባዋል ብለን እናምናለን፡፡

ይህን ሁኔታ ግምት በማስገባት የሞግዚት ወይም አስቸኳይ መንግስት ማቋቋምን አስፈላጊነት ከአሁኑ ሊታሰብበትና ሊሰራበት ይገባል የሚል እምነት አለን። ስለሆነም የሞግዚት መንግስት ምን እንደሆነና በምን መልክ መቋቋም እንዳለበት ከዚያም ቀጥሎ ወደ ሽግግር መንግስት የሚተላለፍበትን መንገድ ለማሳየት እንሞክራለን።

**የሞግዚት አስተዳደር ማለት፣**

- ቋሚ ወይም የሽግግር ጊዜ መንግስት እስከሚቋቋም ጊዜ ድረስ ስልጣን የሚረከብ አካል ማለት ነው፤
  - በምዕራቡ ዓለም፣ ይህን መሰሉ አካል፣ በምርጫ ጊዜ፣ ወይም ጥምረት ፈጥረው ስልጣን የያዙ ፓርቲዎች በአብሮነት መስራት ሲያቅታቸውና አንድ ፓርቲ ብቻውን በፓርላማ ውስጥ ስልጣን ይዞ መቀጠል ህጋዊ ሁኔታው የማይፈቅድለት ሲሆን፣ አዲስ ጥምረት ወይም ሌላ ምርጫ ተካሂዶ ሁኔታው እስኪስተካከል ድረስ የሞግዚት አስተዳደር ተቋቁሞ የመንግስትን ስራ ያካሂዳል፣ ወይም፣
  - በፓርላሜንታዊ አሰራር የሚመራ ሀገር ውስጥ፣ ስልጣን ላይ ያለው መንግስት በፓርላማ አባላቱ ቅቡልነት ማጣቱ በድምጽ መንፈግ ሲረጋገጥ (vote of no confidence) ፣ መንግስት ይፈርስና አዲስ ምርጫ እስከሚካሄድበት ጊዜ ድረስ በሞግዚት አስተዳደር ይተካል፣ ወይም ራሱ ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወደ ሞግዚት አስተዳደርነት ይቀየራል፣
  - ከሽግግር ጊዜ መንግስት በተለየ ሁኔታ፣ የሞግዚት መንግስት አካታች እንዲሆን አይጠበቅበትም፣ እንደየሀገሩ ሁኔታ የሞግዚት መንግስቱ በሀገሪቱ ንጉስ/ንግስት፣ በፕሬዚዳንቱ፣ ወዘተ፣ ሊሰየም ይችላል፡፡
  - ወይም፣ በግብጽ ውስጥ የፕሬዚዳንት ሞርሲ መንግስት እንደተገለበጠ እንደሆነው፣ ታዋቂ የሀገሪቱ ምሁራን የሞግዚት መንግስቱን በመሰየም ያደረጉት አሰራርን መከተል ይቻላል፣ በአጭሩ፣ የሞግዚት መንግስት ውሱን ኃላፊነት ብቻ ሲሆን የሚሰጠው፣ አሰያየሙ ብዙ የሚያከራክር አይደለም፡፡የሞግዚት መንግስት ሥልጣንና ተግባራት

**የሞግዚት መንግስት ሥልጣንና ተግባራት**

- የሞግዚት መንግስቱ ግፋ ካለ ለ180 ቀናት አለበለዚያ ለ90 ቀናት ብቻ ስልጣን ይዞ የሚቆይ ይሆናል።
- ይህን መሰሉ የሞግዚት መንግስት በሌሎች ሀገራት ስራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ ሁሉም የየራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በጠየቀው መሰረት ተቋቁመዋል፡፡ ኢትዮጵያም የሀገሪቱ ሁኔታን ተከትላ የምትመሰርተው ሊሆን ይችላል፣ ለምሳሌ

  - ይህ አካል የተለያዩ የተደራጁ አካላት ገና ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት አድርገው በስምምነት ሊፈጥሩት የሚችሉት ሊሆን ይችላል፣
  - በተለያየ ምክንያት ያን ማድረግ ሳይቻል ከቀረ፣ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ይበልጥ የተደራጁ እና ኃይል ያላቸው አካላት ኃላፊነት ወስደው(ተረክበው) ሀገሪቱን በሞግዚትነት ሊያስተዳድሩ ይችላሉ፣
  - እንደተጠቀሰው፣ ኢትዮጵያ ለአንድ ቀንም ቢሆን መንግስት አልባ መሆን የለባትምና፣ ገና ከወዲሁ፣ የሞግዚት አስተዳደሩ ዋና ዋና ተግባሮች ተለይተው መታወቅ አለባቸው፣ እነሱም፣

- ይህ አካል የሚቆይበት ጊዜ ይፋ ያደርጋል
- ይህ አካል በስልጣን ላይ በሚቆይባቸው ጊዜያት የሚያከናውናቸውን ጉዳዮች ለህዝቡ ይፋ ያደርጋሉ፣

ከዐበይት ስራዎቹ መሀከልም፣

- ኢትዮጵያን ከውጭ ጥቃት ለመከላከል፣ ሌሎች ኃይሎችን ባካተተ መልኩ የመከላከያ ኃይሉን አዘጋጅቶና አደራጅቶ መንቀሳቀስ፣ ለዚህ ስራም፣ በወንጀል ያልተሳተፉ በብልጽግና መንግስት ስርየነበሩ ወገኖች የተሃድሶ ስራዎች ካከናወኑ በኋላ ተሳታፊ ሊሆኑ እንዲችሉ መርዳት፣
- ኢትዮጵያን ለመከላከል የሚያካሂዳቸው ዝግጅቶች ካልተሳኩ፣ ወይም በቂ ሆነው ካልተገኙ፣ የአፍሪቃ ህብረት ድጋፍን ሊጠይቅ ይችላል፣
- በመከላከያው ውስጥ ከሚሳተፉ ኃይሎች ውጭ የሚገኙ የታጠቁ ኃይሎች ጋር የሰላም ድርድር አካሂዶ፣ ቋሚ አሰራር እስከሚነደፍ ድረስ ካምፕ እንዲገቡ ያደረጋል፣
- መንግስት ሲንኮታኮት ዝርፊያና ግድያ ሊበረታ ስለሚችል፣ ሳይውል ሳያድር በህብረተሰቡ ንቁ ተሳታፊነት ላይ የተመሰረቱ የሰላምና መረጋጋት አካላት በመላ ሀገሪቱ ማቋቋም ሌላው ተግባሩ ይሆናል፡፡ በዚህ ስራም እንደ እድር የመሳሰሉ ተቋማት ሊያግዙ ይችላሉ፣
- እነዚህ አካላት ህጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው ተደርጎ ስራቸውን ያከናውናሉ፣

  - የማያሻማና ግልጽ መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል፣
  - ሙስና እና ሌሎች አስከፊ ችግሮች እንዳይከተሉ እነዚህ አካላትን የሚቆጣጠር የበላይ አካል ይመደባል፣

- በብልጽግና መንግስት ውስጥ በበላይ ኃላፊነት ሲሰሩ የነበሩ ገለል ተደርገው፣ መንግስት የዕለት ከዕለት ስራውን ሳያቋርጥ መቀጠል አለበት፣
- እንደአስፈላጊነቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተነስቶ ዜጎች የነፃነት አየር እንዲተነፍሱ ማድረግ ያስፈልጋል፣
- በፖለቲካ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ምክንያት የታሰሩ ሁሉ ጉዳያቸው በፍጥነት እየተጣራ ይለቀቃሉ፣

- የሞግዚት አስተዳደሩን የማይመለከቱ ኃላፊነቶች፣

  - ጊዜያዊ እንጂ ቋሚና ዘላቂ ህጎች አያወጣም፣
  - ህገ መንግስት አያሻሽልም፣ አይሽርም፣ በጀት አያወጣም፣
  - ከውጭ መንግስታት ጋር አዲስ ስምምነት አያካሂድም፣ ገንዘብ አይበደርም
  - መንግስት ለማስተዳደር ከሚያስፈልጉት በላይ ቋሚ ኃላፊዎች አይመድብም፣

- ከላይ እንደተገለጸው የሽግግር ጊዜ መንግስቱ እንዲቋቋም የሚያስፈልጉትን ኮሚቴዎች በማቋቋም እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

  - በሽግግር መንግስቱ ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉ ኃይሎችን በመለየት የምክክር ስብሰባዎች ያካሂዳል፣
  - የሽግግር መንግስቱ ፍኖተ ካርታ ረቂቅን በማዘጋጀት እርዳታ ያደርጋል፡፡